# ሊብያን መውደድ...
## <u>ልብ ያለው መሪ ቢገኝ</u>

ምን መጣ፣ ምነው፡ ምነው?
ሊብያን ማፍቀር፣ ዛሬ ነው፣
እንዴት ቢባል? መቸ ጠገነና፣
ቁስላችን ደርቆ ሳይድን ገና!
የሸዋየጋ በደል ሳይረሳ፣
ዳግመኛ ጥላቻ ይነሳ!
በሠላሳ ወገኖቻችን
ዛሬ ደግመው በደሉን
እንደ በግ አንገታቸውን በቢላ
እያሉ፤ "ቢስሚላ፣ ቢስሚላ!"
ልብ ያለው መሪ ካገኘን
...ምን አለ? አሁንስ ቢሆን?
ዕብደት ነው! አውሎ ንፋስ ውሽንፍር
ታሪኩን ከወዴት እንጀምር?
ከሸዋየጋ፣ የጋዳፊ የልጅ-ልጅ ሞግዚት?
ውሃ አፍልተው የቀቀሏት!
የጠበሷት፣ የለበለቧት!
ወይስ ከጋዳፊ አያት፣ ቅድመ አያት?
ነገር ከጀመሩ ጠልቆ፣ ወርዶ ከስሩ
ካልመረመሩ - መች ይገኛል ምስጢሩ!
ልብ ያለው መሪ ካገኘን
...ምን አለ? አሁንስ ቢሆን?



የጋዳፊ ልጅ ሚስት እኮ ነች
ሸዋየጋን በእሳት ያቃጠለች
ባሏም አንድ መልከ ጥፉ
መስሏቸው በስም ሊደግፉ
ሃኒባል አሉትና ዓረፉ!
ያም ሁሉ ሆኖ በትዕግሥት
ማፍቀር እንጂ አይገባም መጥላት!
በአፍሪካ መሬት ጥንት
ሊብያ ከመፈጠሯ በፊት
ቅድመ ክርስቶስ ፪ መቶ ዓመት
በዚያ ቦታ ታላቅ ጀነራል
የሃሚልካር ልጅ ሃኒባል
አፍሪካውያን ወታደሮቹን ይዞ
በተራሮች፣ በባሕር ተጉዞ
ግመሎች፣ ፈረሶች፣ ዝሆኖችም ጭኖ
በኤውሮጳ ዘመተ፣ ሮማ ላይ ጨክኖ...
መንገዱም፣ ዘመቻም ደህና ተሳክቶለት፣
ሮማን አሸንፎ ለዓስራ አምስት ዓመት
ገዛ አምበርክኮ በታላቅ ጀግንነት።

ታድያ የዚያ የታላቁ ጅግና ስም
በጨምላቃ ሰው ላይ ኣያምርም!
...ምን ኣለ? ኣሁንስ ቢሆን?
ልብ ያለው መሪ ካገኘን
ፍቅር እንድናስተምራቸው
እንሂድ ወደ ኣገራቸው...
ቀን የሰጠው ቅል ድንጋይን ያለፋል...
ከፋም፣ ደጉም ዘመን ቶሎ ያልፋል
የጋዳፊ ቅድመ ኣያቶች ከዓረብ መጡና
ጨካኝ ክንዳቸውን በኣፍሪካዊው ዘረጉና
ጥቁሩን ሕዝብ በጠቅላላ ኣውድመው
መላ ኣገሩን ወረሩት ኣግድመው።
ታድያ ከክፋትና ከጭከና
ተራብተው መች ረቡ በጤና?
ኣርሰውም ኣያበቅሉ!
የኣዲስ ኣበባ ከተማንም ኣያህሉ!
ከዘይትና ከትብያ
ምድረ-በዳ ነው ሊብያ...
ከሞላ ጐደል ሕዝባቸው
ስድስት ሚልዮን ነው ቁጥራቸው!
ከሰማንያው ሚልዮን ሕዝባችን፣
ዓስር ሚልዮን ብቻ ኣደራጅተን
ፍቅር እንድናስተምራቸው
እንላክ ወደ ኣገራቸው...
እስላምና ክርስትያን ተባብረን፣
እጅ-ለእጅ ተያይዘን
እናሳያቸው ኣብሮ መኖርን!
ሃይማኖት ሊያስለውጠው
ማንም ማንን ሳያርደው...
ሕይወት ትርጉሙ እንዲገባቸው
በፍቅር እናጥለቅልቃቸው!
እንደ ባልና ሚስት ግብ-ግብ
ይዘን በፍቅር ዱላ ቾብ-ቾብ...
በውድ ነው እንጂ መች በግድ
ኣብሮ መሥራትና መነገድ...
ለዚህ ነው ሊብያን መውደድ፣
ማፍቀር ይገባል ያልነው
መሪ ካገኘን ልብ ያለው!
...ምን ኣለ? ኣሁንስ ቢሆን?
ተነስቶ የሚመራን
ጀግና መሪ ካገኘን
እንሂድ ተነስተን!

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**